# ከመንግስት ግዥ አፈጻጸም ጋር በተያያዘ በተደጋጋሚ የሚቀርቡ ዋና ዋና ጥያቄዎች

---

ጥ. 1 የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ ተግባርና ኃላፊነት ምድን ነው? የተፈጻሚነት ወሰኑስ?

መ. የመንግስት ግዥና ንብረት አስተዳደር ኤጀንሲ በማቋቋሚያ አዋጅ 649/2001 አንቀጽ 15 መሠረት የተሰጡት ተግባራት ከፌዴራል መንግስት መ/ቤቶች የግዥ አፈጻጸምና የንብረት አስተዳደር ሥራ ጋር በተያያዘ የተቆጣጣሪነት ተግባር የሚያከናውን የመንግስት ተቋም ሲሆን የተፈጻሚነት ወሰኑም በአዋጁ አንቀጽ 3 በተገለጸው መሠረት በማናቸውም የፌዴራል መንግስት ግዥ እና ንብረት አስተዳደር ላይ ብቻ ነው፡፡

---

ጥ. 2 ኤጀንሲው ግዥ የመፈጸምና ንብረት የመሸጥ ተግባርን ያከናውናል?

መ. ኤጀንሲው በአዋጅ 649/2001 አንቀጽ 15 ተለይተው የተሠጡትን ተግባራት ከመፈጸም ውጭ የሌሎች መ/ቤቶችን ግዥ የመፈጸምና ንብረት የመሸጥ ተግባር አያከናውንም፡፡

---

ጥ. 3 ለአገር ውስጥ ተጫራቾች በሚወጣ ብሔራዊ ጨረታ የውጭ አገር ተጫራቾች መሳተፍ ይችላሉ?

መ. አዎ፣ የውጭ አገር ተጫራቾች የአገር ውስጥ ተጫራቾች እንዲያሟሉ የሚጠየቁትን መስፈርቶች እስካሟሉ ድረስ በጨረታው መሳተፍ ይችላሉ፡፡ በብሔራዊ ጨረታና (NCB) በአለም አቀፍ ጨረታ (ICB) መካከል ያለው ዋና ልዩነት የጨረታ ማስታወቂያ የሚወጣው በአለም አቀፍ ደረጃ ጥቅም ላይ እየዋለ በሚገኘው የእንግሊዝኛ ቋንቋ እና በእንግሊዝኛ በሚታተም ጋዜጣ ሲሆን እንደአስፈላጊነቱ የጨረታ ዋጋ የሚቀርብበትና ክፍያ የሚፈጸምበት የገንዘብ ዓይነትም አለም አቀፋዊ ተቀባይነት ያገኘ የውጭ አገር ገንዘብ ከመሆኑ በስተቀር ሌሎች አፈጻጸሞች በአብዛኛው ተመሳሳይ

ባህርይ ያላቸው ናቸው:: ስለሆነም ማንኛውም ፈቃደኛና መስፈርቱን የሚያሟላ የውጭ አገር ተጫራች በብሔራዊ ጨረታ ሊሳተፍ ይችላል::

---

ጥ. 4 ማንኛውም የመንግስት መ/ቤት በኤጀንሲው በጋራ ግዥ እንዲፈጸምባቸው የተለዩትን ዕቃና አገልግሎት በራሱ ግዥ መፈጸም ይችላል?

መ. አይችልም፤ በሁሉም /በተወሰኑ መ/ቤቶች በጋራ የሚፈለጉ ዕቃና አገልግሎቶች ተብለው በኤጀንሲው የተለዩትን ዕቃ ወይም አገልግሎት ግዥ የሚፈጽመው በአዋጅ 649/2001 አንቀጽ 60 መሠረት የተቋቋመው አካል ብቻ ይሆናል:: መ/ቤቶች በኤጀንሲው የተለዩትን ዕቃና አገልግሎቶች ዓመታዊ ፍላጎታቸውን በወቅቱ በመለየት ግዥ ለመፈጸም ለተቋቋመው አካል ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል::

---

ጥ.5 በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ በአቅራቢነት መመዝገብ ግዴታ ነው? ግዴታ ከሆነ የአመዘጋገቡ ሄደት እንዴት ነው?

መ. አዎ ግዴታ ነው:: በተለየ ሁኔታ ከሚፈቀደው በስቀተር በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ አቅራቢዎች የመመዝገብ ግዴታ አለባቸው::

ሀ. የአመዘጋገብ ሂደቱም፣

- በዕቃና አገልግሎት ፣በግንባታ ሥራ እንዲሁም በምክር አገልግሎት አቅራቢነት የተሰማሩ ግለሰቦችና ድርጅቶች በኤጀንሲው ድረ-ገጽ ላይ ራሳቸውን መመዝገብ አለባቸው:: በአዲሱ የምዝገባ አሠራር ከዚህ በፊት ኤጀንሲው ወይም ሥራና ከተማ ልማት ድረስ በግንባር በመቅረብ የተመዘገቡትንና የምስክር ወረቀት የወሰዱትን ጨምሮ ሁሉም በመንግስት ግዥ ለመሳተፍ የሚፈልጉና ፈቃደኛ የሆኑ አቅራቢዎች በሙሉ መመዝገብ አለባቸው::

ለ. በአቅራቢነት ለመመዝገብ መሟላት ያለባቸው ሁኔታዎች:_

1. አቅራቢው የተሠማራበትን የሥራ ዘርፍ የሚገልፅ የታደሰ ንግድ ፈቃድ፣

2. የምክር አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሰማራ አቅራቢ ከሆነ ስለተሰማራበት የሙያ ዘርፍ በሚመለከተው አካል የተሰጠ የሙያ ብቃት ማረጋገጫ ማስረጃ፣
3. በግንባታ ሥራ ላይ የተሰማራ ከሆነ የሥራ ተቋራጭነት ሥራ እንዲሠራ በሥራና ከተማ ልማት ሚ/ር የተሠጠውን ደረጃ የሚገልፅ ማስረጃ፣
4. የተሽከርካሪ ጥገና አገልግሎት በመስጠት ሥራ ላይ የተሠማራ ከሆነ ከፌዴራል ትራንስፖርት ባለስልጣን የተሠጠ ደረጃውን የሚገልፅ ማስረጃ፣
5. መድሐኒት እና የህክምና መገልገያ መሳሪያዎችን በማቅረብ የተሠማራ ከሆነ ከምግብ፣ መድሐኒትና የጤና እንክብካቤ አስተዳደርና ቁጥጥር ባለስልጣን የተሠጠ ማስረጃ፣

ያላቸው መሆን አለባቸው::